★ዴሞክራሲያ★

ቅጽ:2 ቁጥር 18 መስከረም 24 ቀን 1968 ዓ.ም.

ያኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፖርቲ ልሣን::

በሥልጣን ጥም የሰከረ፣ ስለ ሰፊው ሕዝብም ሆነ ስለሀገሪቷ ምንም ዓይነት ጠላፊነት የማይ ሰማቸው ፋሽስት ምርጥ መኰንኖች፣ የሠፊውን ሕዝብ መሠረታውያን ጻሞክራሲያውያን መብቶችን በመገ ፈፍ፣ ሰላማውያን ሠራተኞችን በመረሽን: ሰብአዊ ርሕራጤ የተለየው፣ የሕገ ልጋም የማያውቅ: የጭቆና ሥርዓዝ በአገሪቷ ላይ በመዘርጋት ሳብ አደረን ጠቅላላ የሥራ ማቆም እርምጃ እንዲወስድ አስገድደውታሉ::-

ሳብ አደረ ይህንን የሥራ ማቆም እርምጃ እንዲወስድ የተገደደው ከቀየው ብዝብዛ በላይ፣ ለነጻነተና ለሕይወቱ ምንም ዋስትና የማይሰጥ፣ ምንም ዓይነት አማራጭ የማይተው አምባገነናዊ አመጽ በሌዩ ላይ ስለተዘረጋበት መሆኑ ለማንም ገልጽ ነው::

ሳብአደረ የጠየቃቸው ጥያቄዎች፣ የመላው ሠፊ ሕዝብ ጥያቄዎች ናቸው:: የጥያቄዎቹ ትክክ ለኛነት ለማንም ተራማጅ ብቻ ሳይሆን ለማንም ጻሞክራት፣ ለማንም የሠፊውን ሕዝብ ወገን መጨቆን ና መረገጥ ለሚጠላ ለማንም ሰዎች አለምክንያት መረሽን የለባቸውም ብሎ ለማያምን ገልጽ ነው:: በአጭረ ጥያቄዎቹ የሚያከራክረ አይደሉም::

ግን ለነዚህ ጥያቄዎች የምርጥ መኰንኖች መንግሥት ምን ዓይነት መልስ ሰጠ ፤ ለጥያቄዎቹ ከምርጥ መኰንኖች መንግሥት የተሰጠው መልስ፣ አብሪታዊና ፋሽስታዊ ብቻ ሳይሆን ሞቱንና ውድቀቱ ን በህዝብ ደምና አልቂት ሊሸፍን፣ ያለቀና የደቀቀ ህላዊውን በጠመንጃ ሊከለክል የሚሞክር የተስፋ ቢስ መንግሥት መልስ ነው::

<u>ሰፊው ህዝብ ሆይ:</u> የምርጥ መኰንኖች መንግሥት ነኝ የሚለው የወንበዴዎች ቡድን፣ አስከዛሬ ድረ ስ የተወሰነ መብት ያለህ መሆኑን፣ ሕገና ስርዐት መኖሩንም በቃል ደረጃ ተቀብዩ፣ ሕጉን በመተ ላለፍ ስረሽንህ ነበረ:: ከዛሬ ጀምሮ ግን መጨቆን መረሽን በኃይል ማስራት ሁሉን በአዋጅ ሕጋዊ አደርገዋለሁ:: አስከዛሬ ድረስ መረሽኑ የግሌ ሥልጣን ነበረ:: ከአንግዲህ ወዲህ ግን አያንዳንዱ መለዩ ለባሽ በማሰር በመዘረፍ በመረሽን የወንጀሌ ተካፋይ እንዲሆን አስገድደዋለሁ፡ ብሎዋል:: መስከረም 19 የወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ትርጉሙ ይህ ነው::

<u>ሳብ አደር ሆይ:</u> አሁንም የምርጥ መኰንኖች ቡድን ምንም ዓይነት አማራጭ መንገድ አልተወልህም:: መሠረታውያን መብቶችህን በጠየቅክ፣ ዳቦና መጠለያ በፈለግህ፣ በየመንገዱ አለምክንያት መረሽን የለብኝም በአልክ፣ ይበልጥ እጨቁንህ አለሁ፣ ይበልጥ አስርህአለሁ፣ ይበልጥ እርሽንህአለሁ፣ በአዋጅ ሁልህንም ወንጀለኛ ብዬአለሁ፣ ሁልንም መታሰር መረሽን አለብህ ብየህአለሁ:ብሎዋል:: በአንድነት ቁም:: ወደፊት ግፋ፣ ታቸንፋለህ፣ ነጻነትህን በትግልህ ታገኛታለህ፣ ደግሞ ማንም ሊንጥቅህ አይቸልም::

<u>ሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ:</u> የሳብ አደረ ጥያቄዎች የያንዳንድህ ጥያቄዎች ናቸው:: ከሳብአደ ረ ጋር በአንድነት ቁም:: አብረህ ታገል፣ ችግሩን አብረህ ተካፈል፣ ድሉንም አብረህ ትካፈላ ለህ::

<u>የመንግሥት ሠራተኞች:</u> ለምርጥ መኰንኖች ቡድን መሣሪያ አትሁኑ፣ ሥራ በማቆም ከሳብ አደረ ጋር ተሰለፋ::

<u>ወጣት ዘማቸችና ተማሪዎች:</u> ስተታገሉለት ለቀያቸሁት ለሳብአደረ ድኅንነትና ነጻነትና፣ ለሠፊው ሕዝብ መብት ከሳብአደረ ጉን በአንድነት ተሰለፋ:: በቆራጥነት ታገሉ::

<u>የኢት ጵጵያ ሠፊው ወታደር ህዝ:</u> በየካቲት 1966 ዓ.ም. የኃይለሥላሴ ፊውዳል ቡርጃ መንግሥት ከንዱህን በመደብ ጋደኖህ፣ በላብአደሩና በአርሶአደሩ በአጠቃላይ ለሠፊው ሕዝብ ላይ አንድታነሳ በጠየቀበት ጊዜ አምቢ ብለህ ከሠፊው ሕዝብ ጋር ቆመሀል:: ከተከፈለከው አርሶ አደር አባትህ፣ በስጋና በደም ከሚዛመዱህ ላብ አደሮችና ተራማጅ ምሁራን ጋር ሆነህ ህዝባዊ ስርዐት ለመመስረቱ ለዚህም ለመታገል በቆምክ በሰዎችና በአሳማህ ተሰለፍክ ያሉ ምርጥ መኮንኖች ከአንተና ከህዝቡ ጀርባ ቁመ አሉ:: ከሰፊው ሕዝብና ካንተም ጭምር ቀስ በቀስ ከተነጠሉ በኋላ፣ የቀምከለተን ላብ አደር አንድተጨፈጭፍ፣ በወንድሞችህ በአህቶችህና በልጆችህ በጉረቤቶችህም ደም አንድታጠብ አስከመጠየቅ ደርሰዋል:: ይህ ሁሉ ለምን የምርጥ መኮንኖች ቡድን የሠፊውን ሕዝብ ፍላጐት በመጣስ፣ የሠፊውን ሕዝብና የአንተንም መብት በመርገጥ አምባገነናዊ የግል ሥልጣን ለመመስረት፣ ባለቸው ፀረ-ሕዝብ አላማ ምክንያት ነው:: ሠፊው የኢት ዮጵያ ወታደር፣ የበታች ሹማምንትና ተራማጅ መኮንኖች የምርጥ መኮንኖች ቡድን የወንጀል ተግፋይ አትሁኑ፣ ከመደብ ጋደኞቻችሁ ከላብ አደሮች፣አርሶ አደሮች፣ ተራማጅ ምሁራን፣ከዘማቾች፣ ከተንገሽ ነጋዴዎች፣ከሥራ አጦች ወዘተ.... ጐን ተሰለፋችሁ፣ ለነጻነት ለዕድገት፣ ለአኩሉነትና ለዲሞክራሲያዊ አንድነተ ታገሉ::

የአስቸኳይ ጊዜው አዋጅ ተነስቶ የሠፊው ሕዝብ መሠረታውያን ዲሞክራሲያውያን መብቶች ይከበሩ፣ ላብአደሮች ያቀረቡት ተከከለኛ ጥያቄዎች ይፈጸሙ:: የታሰሩት መምህራን ዘማቾች ወታደሮች ሌሎችም ተራማጅ የፖለቲካ አስረኖች ይፈቱ::

በመጨረሻም አሁን ያለው የምርጥ መኮንኖች ቡድን ሰያባባሰው የሄደው የተደራረበ ችግር መጨረሻ መፍትሔ ሊያገኝ የሚችለው የሕዝብ አምነትና ድጋፍ ያለው፣ ከሁሉም የሠፊው ሕዝብ ወገኖች የተውጣጣ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ሲቋቋም መሆኑ ግልጽ ነውና፣ ከተደራጁት የፖለቲካ ፖርቲዎችና ቡድኖች፣ከኢ.ሠ.አ.ማ.፣ከገበሬ ማኅበሮች፣ከመምህራን ማኅበር፣ በዲሞክራሲያዊ ዘዴ ከመረጡ የጠር ኃይሎች ወኪሎች አንዲሁም ከሌሎች የሠፊው ሕዝብ ወገኖች የሚውጣጡ ህዝባውያንን ያቀፈ ከአነሱ ብቻም የተያዘ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም:: በህገሪቱ ያሉ ተራማጅ ቡድኖች፣ ፀረ-ፈውዳል፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት፣ ፀረ-ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊና ለዲሞክራሲ ያቆሙ ፖርቲዎች ሁሉም ለዚህ ግብ የአንድነት ዘንዳቸውን ያነሱ፣ ህብረታቸውንም በጋራ ኘሮግራም፣ በጋራ መስመርና በጋራ የትግል ሰልት ያስተባብሩ::

ሠፊው ህዝብ ያሸንፋል ::